መልዕክት/ስብከት:
<u>እናንተ የእግዚአብሔር መቅደስ ናችሁ</u>

Sermon: Y'all Are God's Temple

ለጥር 31, 2021 ለሚቀርብ

መጋቢ ክሪስ ሲክስ

የአንድ ድምጽ ሕብረት

የቅዱሳት መጻሕፍት ንባብ

Scripture Reading

1ኛ ቆሮ. 3:5-17

1 Corinthians 3:5–17

አጵሎስ እንግዲህ ምንድነዉ? ጳዉሎስስ ምንድነዉ?በእነርሱ እጅ ያመናችሁ አገልጋዮች ናችሁ ለእያንዳዳቸዉም ጌታ እንደሰጣቸዉ ያገላግላሉ። እኔ ተከልኩ አጵሎስም አጠጣ፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ያሳድግ ነበር። እንግዲያስ የሚያሳድግ እግዚአብሔር እንጂ፣ የሚተክ ቢሆን ወይም የሚያጠጣ ቢሆን አንዳች አይደለም። የሚተክልና የሚያጠጣ አንድ ናቸዉ። ነገር ግን እያንዳንዱ እንደራሱ ድካም መጠን የራሱን ደመወዝ ይቀበላል። የእግዚአብሔር እርሻ ናችሁ፣ የእግዚአብሔር ሕንፃ ናችሁ ከእርሱ ጋር አብረን የምንሠራ ነንና።

የእግዚአብሔር ፀጋ እንደተሰጠኝ መጠን እንደ ብልሃተኛ የአናጺ አለቃ መሠረትን መሠረትሁ፣ ሌላዉም በላዩ ያንፃል። እንዳንዱ ግን በርሱ ላይ እንዴት እንዲንጽ ይጠንቀቅ። ከተመሠረተዉ በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልምና። እርሱም ኢሱስ ክርስቶስ ነዉ። ማንም ግን በዚህ መሠረት ላይ በወርቅ ቢሆን፣ በብር፣ በከበረ ድንጋይም፣ በእንጨትም፣ በሣርም ወይም በአገዳ ቢያንጽ የእያንዳንዱ ሥራ ይገለጣል። በእሳት ስለሚገለጥ ያ ቀን ያሳያልና፣ የእያንዳንዱም ሥራ እንዴት መሆኑን እሳቱ ይፈትነዋል። ማንም በእርሱ ላይ ያነጸዉ ሥራ ቢጸናለት ደመወዙን ቀበላለል። የማንም ሥራ የተቃጠለበት ቢሆን ቢሆን ይጎዳበታል። እርሱ ራሱ ግን ይድናል። ነገር ግን በእሳት እንደሚድን።

የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደሆናችሁ የእግዚብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታዉቁምን? ማንም የእግዚብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል። የእግዚብሔር ቤተ መቅደስ ነዉና ያዉም እናንተ ናቸሁ።

አስተዋጽዖ

አንደኛ ነጥብ፡ እግዚአብሔር ብቻ ነዉ እድገትን ሊሰጥ የሚችለዉ

Point #1: Only God Gives the Growth

ሁለተኛ ነጥብ፡ አንድ መሠረት

Point #2: One Foundation

ሦስተኛ ነጥብ፡ እናንተ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ናችሁ

Point #3: Y'all Are God's Temple

ይህንን መልዕክት በተለያየ ቋንቋ ለሚያነቡት ጓደኞቻችን ማስታወሻ፡ ያለምንም ግርታ ለመከታተል እንዲረዳችሁ መጋቢዉ በአንድ ጊዜ በአንዱ ጥቅስ ላይ መልዕክቱን ያስተላልፋል። የጥቅሶቹን ቁጥር እያዳመጣችሁ ለመከታተል ይረዷችኋል።

ሦስተኛ ነጥብ፡
እድገትን የሚሰጠዉ እግዚአብሔር ብቻ ነዉ

Point #1: Only God Gives the Growth

<u>ጥቅስ ቁ. 5ሀ፡</u>
አጵሎስ ታዲያ ማነዉ? ጳዉሎስስ ማነዉ?

ጳዉሎስ ወደምዕራፍ 1 ቁጥር 10-12 ተመልሶ እንዲህ ሲል ይጠቅሳል፡

> ነገር ግን ወንድሞች ሆይ ሁላችሁ አንድ ንግግር እንድትናገሩ፣ በአንድ ልብና በአንድ ሃሳብም የተባበራችሁ እንድትሆኑ፣ እንጂ መለያየት በመካከላችሁ እንዳይሆን በጌታችን በኢሱስ ክርስቶስ ስም እለምናችኋለሁ። ወንድሞቼ ሆይ በመካከላችሁ ክርክር እንዳለ ስለእናንተ የቀሎኤ ቤተሰብ አስታዉቀኛልና ይህንም እላላሁ እንዳንዳችሁ እኔ የጳዉሎስ ነኝ፣ እኔ ግን የኬፋ ነኝ እኔስ የክርስቶስ ነኝ ትላላችሁ።

በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ያለዉ ይህ ክፍፍል ጳዉሎስ በዚህ ደብዳቤዉ ትኩረት ካደረገበት ቀዳሚ ጉዳዮች አንደኛዉ ነዉ። ሽክም ያሳደረበት ነገር ለተለያየ መሪዎች ያላቸዉ ታማኝነት ቤተ ክርስቲያንን እንዴት በተለያየ ቡድን ሊከፋፍል እንደቻለ ነዉ። ይህም የፍልስፍና ፉክክር ባለበት የግሪክ ማህበረሰብ የተለመደ ነበር። በነዚያ ት/ቤቶች የነበሩት መሪዎች ተማሪዎችንና ተከታዮቻቸዉን ወደነርሱ ለመሳብ ይሞክሩ ነበር። ይኼን የሚያደርጉት ደግሞ አብዛኛዉን ጊዜ በሌሎች መሪዎች ላይ ትችት በመሰንዘር ነበር።

ያ ደግሞ ክርስቶስ በርሱ ቤተ ክርስቲያን ዉስጥ ሊያይ ከሚጠብቀዉ ተቃራኒዉ ነዉ። ከዚያ ይልቅ ጳዉሎስ አጵሎስና እርሱ ሁለቱም አንድ መሆናቸዉን ይናገራል።

<u>ጥቅስ ቁ.5ለ፡</u>

እግዚአብሔር ለእነርሱ እንደሰጣቸዉ የቤት ሥራ በእነርሱ በኩል ለማመን የበቃችሁባቸዉ አገልግጋዮች ናቸዉ።

አዎን ጳዉሎስና አጵሎስ በቆሮንቶስ ባለች ቤተ ክርስቲያን ዉስጥ ጠቃሚ መሪዎች ናቸዉ። ጀግኖች ግን አይደሉም። አገልጋዮች ናቸዉ - የግሪኩ ትርጉም ዲያኮናይ ይለዋል።

በቤተ ክርስቲያን ዉስጥ ያሉት ዲያቆናት ስያሚያቸዉን ያገኙት ከዚህ ነዉ። ለዲያኮናይ በጣም መሠረታዊ የሆነዉ ትርጉም አስተናጋጅ የሚለዉ ነዉ። እርሱም ለእንግዶች ምግብ በማቅረብ የሚያገለግል ነዉ። ጳዉሎስ ምግቡን ላቀረበዉ ሰዉ ምስጋናና ሆይ ሆይታ አታቅርቡለት እያለ ነዉ። ያዘጋጀዉንም እንደዚያዉ! እግዚአብሔር መልካም እንደሆነ ቀምሳችሁ እዩ!

በቆሮንቶስ ሰዎችን ወደማመን ያመጣቸዉ በጳዉሎስ በኩል የቀረበዉ የእግዚአብሔር ቃል ነበር። እግዚአብሔር የምስራቹን ቃል ለማቅረብ አገልጋዮቹን ይጠቀማል። ነገር ግን እግዚአብሔር ብቻ ነዉ የሰዎችን ልብ በመንፈስ ቅዱስ ሥራ አማካኝነት መለወጥ የሚችለዉ። እርሱም ልጁ በሆነዉ በክርስቶስ እንድናምን እምነትን ይሰጠናል።

በሴሚናሪ በነበረኝ የመጀመሪያዉ ክፍለ ጊዜ በእዉነት እንደተደሰትኩ አስታዉሳለሁ። ምክያቱም በምናጠናዉ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ዉስጥ አንድ ነገር አግኝቼ ነበርና። የፕሮፌሰሬን ትኩረት ለማግኘት እጄን አነሳሁ። ነገር ግን እኔን ከመጥራቱ በፊት አንተ በጣም ጎበዝ እንደሆንክ ታስባለህን የሚል የመንፈስ ቅዱስን ድምጽ እንዳገኘሁ ተሰማኝ? የሰጠሁህን አእምሮ በመጠቀም በባሪያየ እርዳታ በቃሌ ላይ መገለጥ እንደመጣልህ ለፕሮፌሰርህ ማሳየት ትፈልጋለህን?

ለእኔም ሆነ ለሌላዉ የእግዚአብሔር ቃል አገልጋይ ስለአገልግሎታችን መኩራራት፣ በቤተ ክርስቲያናችን ስለሚሆነዉ ነገር ጉራ መንፋት በርግጥ ሞኝነት ነዉ። ጳዉሎስ በቁጥር 6-9 እንዲህ ይላል

<u>ቁጥር 6-7ሀ፡</u>
እኔ ተከልኩ አጵሎስም አጠጣ፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ያሳድግ ነበር። እንግዲያስ የሚያሳድግ እግዚአብሔር እንጂ የሚተክል ቢሆን ወይም የሚያጠጣ ቢሆን አንዳች አይደለም።

እግዚአብሔር ብቻ ነዉ በሙቱ ኃጢአተኛ ልብ አዲስ ሕይወት እንዲያድግ ማድረግ የሚችለዉ። ወንጌልን በምናካፍልበት ጊዜ ይሄ በርግጥ ሁላችንም ለማስታወስ የሚጠቅመን ነገር ነዉ። የምትጸልይላቸዉ ሰዎች አሉ ወይ? እስካሁን ኢየሱስ እንደሚያስፈልጋቸዉ ማየት ያቃታቸዉ ሰዎች ማለታችን ነዉ ?

እንደእኔ ለአንድ ሰዉ ለዘመናት እየጸለይክ ከሆነና እስካሁን ወደክርስቶስ ካልተመለሱ ያንተ ስህተት እንዳይደለ አስታዉስ። ትተክላለህ ታጠጣለህ። ድርሻህን ተወጣ። ነገር ግን እግዚአብሔር ብቻ ነዉ ሙት ልቦች ትንሳኤ እንዲያገኙና ዳግም ልደት እንዲመጣ ማድረግ የሚችለዉ።

እግዚአብሔር የሂደቱ አካል አድርጎ ሊጠቀምብህ ይችላል ወይም ሌላዉን ሰዉ። ያ ምንም አይደለም፣ ምክኒያቱም.....

ቁጥር 8 የሚተክልና የሚጠጣ አንድ ናቸዉ። ነገረ ግን እያንዳንዱ እንደራሱ ድካም መጠን የራሱን ደመወዝ ይቀበላል። .....ከእርሱ ጋር አብረን የምንሠራ ነንና።

ጳዉሎስና አጵሎስ በተመሳሳይ እርሻ ዉስጥ የሚሠሩ ገበሬዎች ናቸዉ። በተመሳሳይ ሕንፃም የሚሠሩ አናጢዎች ናቸዉ። ጳዉሎስና አጵሎስ በቤተ ክርስቲያን ዉስጥ ጠቃሚ መሪዎች ናቸዉ። ነገር ግን ራስን ከሌላዉ ያገለለ ጠቀሜታ የላቸዉም።

የአሌክሳንደሪያ ፕሪስፒቴሪያን ቤተ ክርስቲያን የአንድ ድምጽ ሕብረት ቤተ ክርስቲያን እናት ነች። በዚህ ዓመት የአሌክሳንደሪያዋ ፕሪስፒቴሪያን አዲስ ቤተ ክርስቲያን በመገንባት ላይ ነች። ብዙ ሰዎች በሥራዉ ተሳትፎ ያደርጋሉ።

ግድግዳዉ በሁለት ሰዎች ደህና አድርጎ ከተቀባ፣ አንዱ ሰዉ መቀባቱን የት እንዳቆመና ሌላዉ ደግሞ ይኸንኑ ሥራ ከየት እንደጀመረዉ ማየት የለብህም። የሸክላዉ ግድግዳ አንተ ከምትሠራበት ይልቅ እኔ እሠራ የነበረበት ቦታ የተለየ መሆን የለበትም። መላዉ ቀለም ቀቢዎችና፣ ግንበኞች እንደዚሁም አናጢዎች ከስማቸዉ ወይም ከዝናቸዉ የበለጠ ለሚጠናቀቀዉ ሥራ መጠንቀቅ ይኖርባቸዋል።

ያ ነዉ ጳዉሎስ ሊያነሳ የፈለገዉ ነጥብ። ለእግዚአብሔር ሰዎች ጳዉሎስን ወይም አጵሎስን ሲያሞግሱ ማየት አግባብነት የሌለዉና አጸያፊ ነዉ። ማንኛዉም የፈጸሙት መልካም ሥራ ጳዉሎስ በቁጥር 10 ላይ እንደሚናገረዉ

እግዚአብሔር በሰጣቸዉ ፀጋ ልክ ነዉ።

ስለዚህ ጳዉሎስ ሁላችንም ልብ እንድንል የሚፈልገዉ ክርስቶስንና እርሱን ብቻ እንድንከተል ነዉ። መጋቢዎችና ሽማግሌዎች እንደዚሁም ዲያቆናት መሪዎች ናቸዉ። ነገር ግን እነርሱ በመጀመሪያ ተከታዮች ናቸዉ። መጋቢ መጋቢ ያለዉነዉ። የበለጠ ተሰጥዖ ያለዉ መሪ በመጀመሪያ በበግነት ነዉ የሚታወቀዉ።

ስለዚህ የአገልግሎት ሥራ የእኛ ሥራ አይደለም። ከዚያ ይልቅ እኛ ከእግዚአብሔር ጋር በአብሮነት የምናገለግል ነን። በአንዱ ብቸኛ መሠረት ላይ ነዉ የምንገነባዉ። ያ ሁለተኛዉ ነጥብ ነዉ።

<u>ሁለተኛ ነጥብ፡</u>
አንድ መሠረት

Point #2: One Foundation

<u>ሁለተኛዉ ነጥብ፡</u>
ቁጥር 10ለ-11 እንደብልሃተኛ የአናጺ አለቃ መሠረትን መሠረትኩ ሌላዉም በላዩ ያንጻል። ..... ከተመሠረተዉ በስተቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልምና እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነዉ።

ራሱን እንደብልሃተኛ የአናጺ አለቃ በመቁጠሩ ጳዉሎስ በኩራት መንፈስ ራሱን ከፍ ያደረገ ይመስላል። በነዚህ ቃላት ማንንም ለማስደመም ፈልጎ እንደሆነ አላስብም። በቆሮንቶስ ያለዉን ቤተ ክርስቲያን ያስጀመረዉ እርሱ ነዉ። ቤተ ክርስቲያን ተካይ ነበር። በቆሮንቶስ ያሉት የመጀመሪያዎቹ አማኞች ጳዉሎስ ወንጌሉን ያካፈላቸዉ ናቸዉ። በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ግድግዳ በመጀመሪያ ተርታ የነበሩ አለቶች ናቸዉ።

በዚህ ቦታ የተጠቀማቸዉ የግሪኩ ቃላት የአናዊዉንና የተቋራጩን ሁለቱንም ተግባር ያካትታል። ጳዉሎስ ይህን ቤተ ክርስቲያን የመትከል ራዕይ ነበረዉ።

እንደዚሁም የመገንባቱንም ከባድ ሥራ በስብከቱ፣ በማስተማር ሥራዉ፣ የቆሮንቶስ ሰዎችንም ደቀመዝሙር በማድረግ ተግባር ተወጥቶታል።

ነገር ግን ጳዉሎስ የቱን ያህል ይድከም ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነዉ መሠረቱና የማዕዘኑ ራስ።

ጳዉሎስ በ1ኛ ቆሮ. 2፡1-2 ባለዉ በዚህ ተመሳሳዩ ደብዳቤ የሚከተለዉን ጽፏል

> እኔም ወንድሞች ሆይ ወደእናንተ በመጣሁ ጊዜ በቃልና በጥበብ ብልጫ ለእግዚአብሔር ምስክርነቱን ለእናንተ እየነገርኩ አልመጣሁም። በመካላችሁ ሳለሁ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር እርሱም እንደተሰቀለ ሌላ ነገር እንዳላዉቅ ቆርጬ ነበርና።

እዉነተኛ ጥበብ፣ እዉነተኛ ሥነ መለኮት፣ እዉነተኛ ቤተ ክርስቲያን ሊኖሩ የሚችሉት በተሰቀለዉና በተነሳዉ በኢየሱስ ክርስቶስ እዉነተኛ የወንጌል መሠረት ላይ መገንባት ሲችሉ ብቻ ነዉ። እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን ያድናል። በእኔ አስተያየት ያ የወንጌሉ ምርጥ የማጠቃለያ ሃሳብ ነዉ።

እግዚአብሔርና እግዚአብሔር ብቻ ነዉ በዘለቄታ መልክና በተሟላ ሁኔታ ማዳን የሚችለዉ። ይህን የሚቀበሉት ማናቸዉም ራሳቸዉን ማዳን የማይችሉ ኃጢአተኞች ናቸዉ። ከዚያ ይልቅ ለኃጢአታችን ይቅርታ በመስቀል ላይ በፈጸመዉ የመስዋዕትነት ሥራ በመታመን ወደኢየሱስ በእምነት ይመለሳሉ። ያንን እዉነት ነዉ ጳዉሎስ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የመሠረተዉ። እርሱም ዛሬ ላለዉ የትኛዉም እዉነተኛ ቤተ ክርስቲያን መሠረት ነዉ።

ወደኢየሱስ በእምነት ከመጣህ ወዲያ አንተ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ሌላዉ አለት ነህ። በዚያዉ መሠረት ላይ ነዉ የቆምከዉ። ወንጌል ከኃጢአት በደልና ሃፍረት ነፃ ሊያደርገን በመቻሉ ኢየሱስን ለመከተልና፣ በአኗኗራችን፣ ለወንድሞቻችንና ለእህቶቻችን በሚኖረን ፍቅር፣ እንደዚሁም ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን መስፋፋት ድርሻችንን በማበርከት እግዚአብሔርን ለማክበር ነፃ ነን።

<u>ቁጥር 10</u>

መሠረትን መሠረትኩ ሌላዉም በላዩ ያንጻል.....እያንዳንዱ ግን በእርሱ ላይ እንዴት እንዲያንጽ ይጠንቀቅ።

ጳዉሎስ አሁን በመሠረቱ ላይ ወደተገነባዉ ይመለሳል። ይህም በሚታይ ሁኔታ ወደተገነባዉ ወደእግዚአብሔር ቤት ማለት ነዉ። እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን እንድናከናዉን በሰጠን አገልግሎት አማካኝነት በክርስቶስ አካል በኩል አድርጎ ቤተ ክርስቲያኑን ይገነባል ያሰፋልም።

በሚስዮናዊነት ወደዉጭ አገር ስለምትሄደዉ አንዲት ወጣት ሴት ታሪክ አንብቢያለሁ። ከመሄዷ በፊት ቤተ ክርስቲያኗ በአምልኮ ክፍለ ጊዜያቸዉ ለርሷ ለመፀለይና ለሚስዮናዊ አገልግሎት ለመለየት ወደፊት ያመጣታል። ክፍለ ጊዜዉ ከተጠናቀቀ በኋላ ሰዎች ወደእርሷ መጥተዉ እንደሕፃን በልጆች ማሳደጊያ ሥፍራ እንደተንከባከቧት ወይም በሰንበት ትምህርት ቤት እንዳስተማሯት ለመናገር ወደፊት መጡ። ሌላዉ በወጣት አመራር ቡድን ዉስጥ የነበረ መሪ ሲሆን ስለሚስዮናዊነት አገልግሎት የተናገራት ነበር። ሌላዉ እንደዚሁ በወጣትነቷ ዕድሜ ደቀ መዝሙር በማድረግ የሠራባት ነዉ። እያንዳንዳቸዉ በዚህች ሚስዮናዊ ሕይወት ያላቸዉን ሁሉ ያበረከቱ ናቸዉ።

እነዚያ የቤተ ክርስቲያን አባላት በጥንቃቄ የግንባታዉን ሥራ አከናዉነዋል። የእነርሱ ታማኝነት የተሞላዉ አገልግሎት በቁጥር 12 ላይ የተገለጸዉ ወርቅና ብር ነዉ።

<u>ቁጥር 10-13</u>

ማንም ግን በዚህ መሠረት ላይ በወርቅ ቢሆን፣ ቡብርም፣ በከበረ ድንጋይም፣ በእንጨትም፣ በሣርም ወይም በአገዳ ቢያንጽ፣ የእያንዳንዱ ሥራ ይገለጣል። በእሳት ስለሚገለጥ ያ ቀን ያሳያልና። የእያንዳንዱም ሥራ እንዴት መሆኑን እሳቱ ይፈትነዋል።

ጳዉሎስ ስለሁለት ዓይነት የሕንፃ መሳሪያዎች ይገልጻል፡ እሳትን መቋቋም የሚችሉትና በቀላል ስለሚቃጠሉት። እርሱም ቤተ ክርስቲያን በዉድ መሣሪያዎች የተገነባ ዉድ ሕንፃ ያስፈልጋታል ማለቱ አይደለም። ይህ ማለት ከትክክለኛ መሠረት የተነሳ በትክክል ራዕይ የተፈጸመ አገልግሎት ማለቱ ነዉ።

ስለሦስት ትናንሽ አሳማዎች የሚያወራ የልጆችን ታሪክ ከማሰብ አልቆጠብም። አንድኛዉ ከገለባ የተሠራ ቤት ገነባ፣ ሌላዉ ከእንጨት፣ ሌላዉ ደግሞ ከሸክላ። ከሸክላ የተሠራዉ ብቻ ነዉ ትልቁ መጥፎዉ ተኩላ በሚመጣበት ጊዜ መቋቋም የተቻለዉ ።

ጳዉሎስ በቆሮንቶስ ላለችዉ ቤተ ክርስቲያን የፍርድ ቀን እየመጣ እንዳለ ያስታዉሳል። እስከዚያ ቀን ድረስ ነዉ በእንጨት የተሠራዉ ቤት መልካም መስሎ የሚታየዉ። በአሸዋ ላይ የተገነባ ቤት ለአሁን ብቻ ይቆማል። ነገር ግን የእግዚአብሔር የፍርድ ዉሃ በሚጎርፍበት ጊዜ፣ ኢየሱስም በጉን ከፍየሉ፣ ስንዴዉን ከገለባዉ ለመለየት በሚመለስበት ጊዜ በስሙ ምን ዓይነት ሥራ እየተሠራ እንደነበር ይፋ ይደረጋል።

<u>ቁጥር 15ሀ, ሐ</u>

የማንም ሥራ የተቃጠለበት ቢሆን ይጎዳበታል፣ እርሱ ራሱ ግን ይድናል። ነገር ግን በእሳት እንደሚድን ይሆናል።

በአእምሯችን ሊኖረን የሚገባዉ ምስል ከሚነደዉ ሕንፃ የሚሸሽዉ ሰዉ ነዉ። ሕይወታቸዉ ይዘዉ አምልጠዋል፣ ነገር ግን ንብረታቸዉ ከእጃቸዉ ወጥቷል፣ በዚያ ቤት ዉስጥ ያከማቹት ሁሉ በእሳት ተቃጥሎባቸዋል።

ደህንነት ዘላለማዊ ነዉ። በርግጥ ከእግዚአብሔር ልጆች አንዱ ከሆንክ ያንን ደረጃህን ከቶ ልታጣዉ አትችልም። ጳዉሎስ የዳኑትን ካልዳኑት እየለየ አይደለም። ነገር ግን የዳኑትን ሰዎች የከበረና ያልከበረ ሥራ በሚል እንጂ።

እርሱ በተለየ ሁኔታ እየተናገረ ያለዉ በቤተ ክርስቲያን ዉስጥ ሥጋዊ ጥበብን ከእግዚአብሔር እዉነት ጋር ስለሚቀላቅሉት መሪዎች ነዉ። እነርሱም ትክክለኛ መሠረት በሆነዉ በኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ነዉ የጀመሩት። ነገር ግን ከዚያም በኋላ ሰዎች ቅድሚያ ከሚሰጧቸዉ ነገሮችና አጀንዳዎች ጋር ይቀላቅሏቸዋል።

ቁልፉ ከመሠረቱ ጋር መቀራረቡ ነዉ። በምትገነባበት ጊዜም በተደጋጋሚ ወደሕንፃዉ ዕቅድ መመለስ ያስፈልጋል። የሕንፃዉ ዕቅድ ወንጌል ነዉ።

ያንን ሁልጊዜ በልባችንና በአእምሯችን በቀዳሚነት መጠበቅ ብንችል ከዚያም የምናከናዉነዉ አገልግሎት እግዚአብሔርን የሚያስከብር ዓይነት ይሆናል። እንደዚሁም አሁንና በፍርድ ቀን ክብርን ያመጣለታል።

<u>ሦስተኛ ነጥብ፡</u>
እናንተ ሁሉ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ናችሁ።

Point #3: Y'all Are God's Temple

<u>ቁጥር 16ሀ.</u>
የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደሆናችሁ .....አታዉቁምን።

ቆሮንቶስ ለተለያዩ ጣዖታት በርካታ ቤተ መቅደሶች የሞሉባት ከተማ ነበረች። ነገር ግን አንዱ እዉነተኛ አምላክ የሚኖረዉ በአንድ እዉነተኛ ቤተ መቅደስ ነዉ። አስተዉል ቤተ መቅደስ የሚለዉ ቃል በቁጥር 16 ላይ በነጠላ ነዉ የተቀመጠዉ። እንደዚሁም በቁጥር 9 ላይ ጳዉሎስ ስለአንድ ሜዳና ስለአንድ ሕንፃ ነዉ እየጻፈ ያለዉ።

ነገር ግን እኛ ሁላችን የተለያዩ ሰዎችና ተለያዩ ግልሰቦች ነን። ለምንድነዉ ጳዉሎስ እናንተ የእግዚአብሔር እርሻዎች፣ የእግዚአብሔር ሕንፃዎች፣ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ናችሁ በማለት ያልጻፈዉ? ምናልባት ሰዎች የእኔ ሰዉነት ቤተ መቅደስ ነዉ ሲሉ ሰምታችሁ ይሆናል።

የኔ ሰዉነት ቤተ መቅደስ ነዉ የሚለዉን በጉግል ላይ ፈልጌ 500, 000,000 የሚደርስ ምላሽ አገኘሁ። በሽዎች የሚቆጠሩ የተለያዩ ቲ ሸርቶች፣ የቡና መጠጫ፣ የሚለጠፉ ምስሎች፣ የዮጋ እስቱዲዎችና አጫጭር ጽሁፎች። ሰዉነቴ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነዉ የሚል ዉስን ነዉ ያጋጠመኝ። አብዛኛዉን ጊዜ ሃሳቡ በእኔ ላይ ያተኮረ ነበር። በርካቶቹ የልምምድ ቲ ሸርቶቹ እንኳን 'የኔ ሰዉነት የኔ ቤተ መቅደስ ነዉ' በማለት በጣም ግልጽ በሆነ መንገድ በራስ ላይ ያተኮሩ ናቸዉ።

ግልጽ መሆን አለብን - የራሳችን ቤተ መቅደስ የሚለዉን ሃሳብ እንወደዋለን። ምክኒያቱም ያ ትክክል ከሆነ እኛ ከሌላ ሰዉ ጥገኝነት የሚያላቅቀን ነዉ። በራሴ ላይ ወይም በራሴና በእግዚአብሔር ላይ ማተኮር እችላለሁ። ምናልባት በእግዚአብሔር አምናለሁ ነገር ግን የተደራጀ ሃይማኖት አልፈልግም የሚሉ ሰዎች ልታዉቅ ትችላለህ። እንግዲህ አዝናለሁ። አንድ ቤተ መቅደስ ብቻ ነዉ ያለዉ። ሁሉም እዉነተኛ የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች በዚያ አንዱ ቤተ መቅደስ ዉስጥ ሕያዉ ድንጋዮች ናቸዉ። እነዚህም ለመንፈስ ቅዱስ የተቀደሰ የመኖሪያ ሥፍራ ለማዘጋጀት እርስ በራስ የተቀናጁ ናቸዉ።

ከጥገኝነት ነጻ የሆንን ክርስቲያን ነን የሚል አነጋገር የለም። ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋር ያለህን የግል ግንኙነት በዉል መቀበል ያለብህ መሆኑ እዉነት ነዉ። እንደዚሁም በሰዉነትህ ላይ ምን ማድረግ እንዳለብህና ለርሱም እንዴት እንደምትጠነቀቅለት ማወቅ ይኖርብሃል። ምክኒያቱም ጳዉሎስ በቁጥር 16 ላይ እንደተናገረዉ፡

<u>ቁጥር 16 ለ፡</u>
የእግዚብሔር መንፈስ እንደሚኖርባችሁ አታዉቁምን?

አንተ በሚለዉ ቃል ላይ ለጥቂት ደቂቃዎች ማተኮር እፈልጋለሁ። እንደእኛ ባለግለሰባዊ ማህበረሰብ 'አንተ' በሚለዉ የብዙ ቁጥር ቅርጽ በሌለዉ ተዉላጠስም በእንግሊዘኛ መናገራችን በእዉነት አለመታደል ነዉ። በዚህ የምንባብ ክፍል ዉስጥ የኔ ሰዉነት ቤተ መቅደስ ነዉ እያለ ጳዉሎስ የሚያስተምርበት አንዱ ምክኒያት ያ ነዉ በሚል ሰዎች ያስባሉ።

የእናንተ ሰዉነት ቤተ መቅደስ አይደለም ብየ ልነግራችሁ በመቻሌ አዝናለሁ። የእናንተ ሰዉነት ሽክላ ነዉ! (ከወረርሽኙ የተነሳ 10 ፓዉንድ በመጨመሬ ይበልጥ እንደ ሽክላ እንደሚሰማኝ አዉቃለሁ)። አንዱን ቤተ መቅደስ ከሚሠሩት ብዙ ሽክላዎች መሃል አንተ በትክክል አንዱ ሽክላ ነህ።

እነዚህን ጥቅሶች በፈረንሳይኛ፣ በአስፓኒኛና በሌሎች በርካታ ቋንቋዎች ብታነብ አንተ የሚለዉን ቃል በምትጠቀምበት ጊዜ ሁሉ የብዙ ቁጥር መሆኑን ትረዳለህ። በአሜሪካ የሚቀርበዉ እኩያ ሁሉንም 'Y'all (አንተ ሁሉም) በሚለዉ ፊደል ይጠቀልለዋል። በአሜሪካ በተለያዩ ቦታዎች ሰዎች 'እናንተ ሁላችሁ' ወይም 'እናንተ ጎበዞች' ወይም ፒትስበርግ በሚባለዉ ሃገር 'ዩዝ (youse)' ወይም ደግሞ 'ይንዝ(yinz)' ::

እነዚህን ቁጥሮች ማንበብ ያለብን እንደዚህ ነዉ፡

ቁጥር 9: የእግዚአብሔር እርሻ ናችሁ፣ የእግዚአብሔርም ሕንፃ ናችሁ፣ ከእርሱ ጋር አብረን የምንሠራ ነንና።

ቁጥር 16: የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታዉቁምን አታዉቁምን? .....የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነዉና ያዉም እናንተ ናችሁ።

በዚህ ምንባብ ክፍል ብቻ ባይሆንም ነጥቡ ይኸዉ ነዉ፣ ነገር ግን በመላዉ መጽሐፍ ቅዱስ ዉስጥ ያለዉ መልዕክት ደግሞ ነዉ። አንዱ ጌታ ለራሱ አንድ ሕዝብ በማለት ይጠራል። በብዙ የእግዚአብሔር ቃል ክፍሎች ይህንን የትኩረት አቅጣጫ እናደምጣለን፡

ኤፌ. 2:22 በእርሱም እናንተ ደግሞ ለእግዚአብሔር መኖሪያ ለመሆን በመንፈስ አብራችሁ ትሠራላችሁ።

1ጴጥ. 2:4 በሰዉም እንደተጣለ በእግዚአብሔርም ዘንድ ግን ወደተመረጠና ክቡር ወደሆነዉ ወደሕያዉ ድንጋይ ወደእርሱ እየቀረባችሁ እናንተ ደግሞ እንደሕያዋን ድንጋዮች ሆናችሁ።

ዘሌ. 26:11 ማደሪያየንም በእናንተ መካል አደርጋለሁ ነፍሴም አትጸየፋችሁም። በመካከላችሁም እሄዳለሁ እኔም አምላክ እሆናችኋለሁ፣ እናንተም ሕዝብ ትሆኑኛላችሁ።

እግዚአብሔር በርካታ ግለሰቦችን አድኗል፣ ነገር ግን ወደአንድ አዲስ <u>የሆነ የሰዎች ስብስብ</u> አድኖናል። ራሳችንን ካማከለ ግለኛነት አዉጥቶ እንደአንድ የቤተ መቅደሱ አካል በሌላዉ ላይ ወዳማከለ ማህበረሰብ አድኖናል።

ለዛሬ አንድ የመጨረሻ ጥቅስ እንመልከት፡

<u>ቁጥር 17:</u>
ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል።

ጳዉሎስ የመቅደሱ አካል እንደሆኑ የሚያስቡ አንዳንድ ሰዎች እንዳሉ ሊያስታዉሰን ይህንን ብርቱ ማስጠንቀቂያ ይጨምራል። የአካሉ አባላት ነገር ግን ያይደሉ።

ከቁጥር 12-14 ያለዉ ማስጠንቀቂያ የተለየ መሆኑን አምናለሁ። ያ ዳግም ለተወለዱት ክርስቲያኖች የተሰጠ ማስጠንቀቂያ ነዉ። ምንም እንኳን የዳኑ ቢሆኑም አገልግሎትን እንዴት እንደሚከታተሉና ቤተ ክርስቲያንን በመገንባት ረገድ ስህተት ሊፈጽሙ ይችላሉ። እነርሱም በፍርድ ቀን ላይ ማንነታቸዉ ይለያል። ነገር ግን ደህንነታቸዉን አያጡም። ምክኒያቱም ቢያንስ ቢያንስ በትክክለኛዉ መሠረት ላይ ጀምረዋልና።

በቁጥር 17 ላይ እየተናገረ ያለዉ ከቶ የአካሉ ክፍል ካልሆኑት ነገር ግን ይልቁንም ቤተ መቅደሱን ለማፍረስ ከሚሠሩት ሰዎች ጋር እንደሆነ አስባለሁ። ዛሬ በቴሌቪዥን መስኮት ከምናያቸዉ የሐሰት አስተማሪዎች አንዳንዶችን አስብ። ብዙዎቹ ትላልቅ ቤት፣ ዉድ መኪናዎች፣ የግል አዉሮፕላን እንኳን ያላቸዉ፣ ባለጠጎች ናቸዉ። ሰዎችን በመዋሸትና ለአገልግሎታቸዉ ገንዘብ እንዲሰጡ በመበዝበዝ ባለጠጎች ሆነዋል።

ቆሮንቶስም ከ200 ዓመታት በፊት እንዲህ ዓይነት ሰዎች ነበሯት። አንዳንዶቹ ታዋቂ ሰባኪዎች ሌሎች ደግሞ የፈዉስ ወይም የትንቢት ስጦታ እንዳላቸዉ የሚሮክሩ ነበሩ። ነገር ግን ተግባራቸዉ የእዉነተኛዉን ቤተ መቅደስ የሚያፈስ ነዉ። ምክኒያቱም የኢየሱስ ክርስቶስን መሠረት በሌላ መሠረት ተክተዋል። ይህም ለገንዘብ ካላቸዉ ስስት፣ ለፖለቲካ ካላቸዉ ዓላማ፣ ዝነኛ ወይም ኃይለኛ ለመሆን ካላቸዉ ጽኑ ፍላጎት የተነሳ ነዉ።

ኢየሱስ እነዚህን ሰዎች በማቴ. 7፡21-23 ላይ፡

> በሰማያት ያለዉን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ፣ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ መንግስተ ሰማያት የሚገባ አይደለም። በዚያ ቀን ብዙዎ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን በስምህስ አጋንንትን አላስወጣንምን፣ በስምህ ብዙ ተአምራት አላደረግንምን ይሉኛል። በዚያን ጊዜም ከቶ አላወቋችሁም እናንተ አመጸኞች ከእኔ ራቁ ብየ እመስከክርባችኋለሁ።

እግዚአብሔር የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌልን መሠረት ለመተካት የሚሞክረዉን ማንኛዉም ሰዉ አይታገስም። ምክኒያቱም .....

<u>ቁጥር 17:</u>
የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ቅዱ ነዉ፣ እናንተም ራሳችሁ ያ ቤተ መቅደስ ናቸሁ።

እዉነተኛዉ የክርስቶስ አካል ቅዱስ ነዉ ምክኒያቱም የአካሉ ክፍሎች በክርስቶስ ደም ታጥበዋል ተቀድሰዋልም። በአንድነት ከበዙ ዳራዎችና ባሕሎች የተገኙ ወንዶችን ሴቶችን እንደዚሁም ልጆችን ያካተተ ቤተ መቅደስ ነን። እንደዚሁም የተለያየ ስጦታና አመላካከት ያለን ነን።

ጥሩ የሚባል የቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ድንጋይ፣ ብረት፣ እንጨት፣ ምንጣፍ፣ ማጣበቂያና ወዘተ. ይይዛል። ሁለንተናዉ ከፕላስተር ብቻ የተሠራ ሕንፃ መቆም አይችልም። ከድንጋይ ብቻ የተሠራ ቢሆን ምቾት አይኖረዉም። እንግዲህ ቤተ ክርስቲያን የሕግ ሰዎች ፣ ቧንቧ ሠራተኞች ፣ መምህራን ወይም ተማሪዎች ብቻ በአባልነት ያሏት ቢሆን ያልተሟላ ነዉ። እያንዳንዱ ሰዉ በተመሳሳይ መንገድ የሚመርጥባት፣ የሚያስብ፣ የሚጫወት ወይም በተመሳሳይ መንገድ የሚሠራ ሰዉ ያሉባት ቤተ ክርስቲያን አንፈልግም።

ይህም በ2020 በአሜሪካችን ካየነዉ የሚያሳዝኑ ነገሮች አንዱ እንደሆነ አስባለሁ። አማኝ ወገኖቻችን በተመሳሳይ ሕንፃ ላይ ያለ ሽክላ፣ የአንዱ አካል አባላት በፀብ ምክኒያት አንዱ ከሌላዉ ጋር ተለያይቷል። የጥቁር ሰዉ ሕይወት ይገደናል የሚል ምልክት የያዙ ሰዎችና መንገዱን አሻግሮ አሜሪካንን እንደገና ታላቅ እናደርጋለን የሚል ምልክት የያዙ ሰዎች ነበሩ። አንድ የሚያደርጋቸዉ ነገር እንደሌለ አስበዋል። ሆኖም በሁለቱም ቡድን ዉስጥ እዉነተኛ የሆኑና የተዋጁ ዳግም ልደት ያገኙ ሰዎች ነበሩ።

እግዚአብሔር በቤተሰብ ዉስጥ ማንን ማቀፍ እንደሚገባዉ በመለየቱ ሥራ ጥበበኛና መልካም ነዉ። አካሉን የተሟላ ለማድረግ የተለያዩ ሰዎችን ይመርጣል ይባርካልም። በዉስጡ ዓይነት ያለዉን ነገር በማካተቱ ጤናማ ነዉ።

ኤፌ. 4: 15... ነገር ግን እዉነትን በፍቅር እዩዝን በነገር ሁሉ ወደ እርሱ ራስ ወደሚሆን ወደክርስቶስ እንደግ። ክርሱም የተነሳ አካል ሁሉ እንዳንዱ ክፍል በልክ እንደሚሠራ በተሰጠለት በጅማት ሁሉ እተጋጠመና እየተያያዘ ራሱን በፍቅር ለማነጽ አካሉን ያሳድጋል።

እግዚአብሔር በስጦታዎችህ፣ በታሪክህ፣ በፍላጎቶችህና በእስተሳሰብህ በጥንቃቄ ሠርቶሃል። ይህም ለአካሉ በተለየ መንገድ አስተዋጽዖ ማድረግና በአካሉም ማገልገል ትችል ዘንድ ነዉ።

ይህ ከዚህ እንድትወስድ የምፈልገዉ በጣም ጠቃሚ ነገር ነዉ። እግዚአብሔር በአንድነት በአንድ ቤተሰብ ዉስጥ፣ በአንድ ቤተ መቅደስ ዉስጥ አኑሮናል። ያም በመካከላችን ለሚገኘዉ ለመንፈሱ ማደሪያ ነዉ። መቅደስ መሆን የምንችለዉ በአብሮነት ብቻ ነዉ። አካል የሆነዉ በአንድነት ነዉ። ከእርሱ ጋር ስንኖር በእኛ ዉስጥና ከእኛ ጋር እንደዚሁም በመካከላችን ይኖራል።

አብረን እንፀልይ፡

ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ የቤተ ክርስቲያን ራስ ነህ። አንተ የማዕዘን ራስ ነህ። የአንተ ሕይወት፣ ሞትህና ትንሳኤህ በአንድነት ያስተሳሰረን እዉነት ነዉ። በዚያ መሠረት ላይ ቤተ ክርስቲያንህን ለመገንባትና ለማሳደግ እንሠራለን። አንድ ቤተሰብ እንደሆንን እንድናስታዉስ እርዳን። አንድ ነን፣ አንዳችን ከሌላዉ ጋርና ካንተ ጋር አንድ ነን። አንተ እንደፀለይከዉ አንድ እንሆናለን። ለቤተ ክርስቲያንህ ደህንነትና ለክብርህ በዚያ መንገድ እንድንኖርና እንድናፈቅር እርዳን። አሜን!